ፖለቲካ

«ስዊዲናውያኑን በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገራችን እንዲገቡ የላከው ተቋም ቢከሰስ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ሊቀጣ ይችላል»

- ዶክተር ገብረመድኅን ስምዖን

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ቤት ዲን

ጌታሁን ዳዲ (ከኢዜአ)

ዓለማችን አሁን ለደረሰችበት ደረጃ የበርካታ ሙያዎች ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ድጋፍ እንዳደረገላት ይታመናል። ለሙያዎቹ የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት መስኮች መሰረት ናቸው፡፡ በትምህርት የበለጸጉት ሙያዎች የየራሳቸው ሥነ ምግባር አላቸው።

የሙያዎቹ ሥነ ምግባር እንዲከበሩ አገሮች በሚያወጧቸው ሕጎችና በትምህርት መስኮቹ የሰለጠኑት ባለሙያዎች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። እያንዳንዱ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር ተከትሎ መሥራት የባለሙያዎቹ ድርሻ እንደሆነም ምሁራን ይገልጻሉ። በተለይ ለሙያው ክብር ሲባል ሥነ ምግባሩን ጠብቆ መሥራት ግዴታ ነው በማለት።

ተጠቃሽ ከሆኑ ሙያዎች መካከል ጋዜጠኝነት አንዱ ነው። ይህ ሙያ የራሱ የሆነ ሥነ ምግባር አለው። ከፍተኛ ኃላፊነትና ጥንቃቄንም ይጠይቃል። የመገናኛ ብዙኃን ተልዕኮዎች የሆኑት ኅብረተሰብን ማሳወቅ፣ ማስተማርና ማዝናናትን ለማሳካት ሙያዊ ሥነ ምግባር ወሳኝነት አለው።

መገናኛ ብዙኃን የሚያገኟቸውን መረጃዎች ከማሰራጨታቸው በፊት መረጃዎቹ ግልጽ፣ ትክክለኛ፣ ሚዛናዊ፣ ተአማኒና ወቅታዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። የሙያውና የባለሙያው ሥነ ምግባር መገለጫዎች እነዚህ ናቸው። በሙያው የተሰማሩ ሰዎች የሚያሰራጩት መረጃ በእውነት ላይ የተመሰረተ ብቻ ሊሆን እንደሚገባው የመስኩ ምሁራን ደጋግመው ያስገነዝባሉ።

ጋዜጠኛው በሚያሰራጨው መረጃ የራሱን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ አልያም ከእውነታው ውጭ ያሉ ነገሮችን አካቶ ማሰራጨትን የሙያው ሥነ ምግባር ፈጽሞ አይፈቅድም። በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችም በዚሁ መርህ ይስማማሉ።

ጋዜጠኞች በአንድ ማዕከል ሆነው ወይም ከአገር አገር እየተዘዋወሩ ሊሰሩ ይችላሉ። ከአገር አገር ተገቢና ሕጋዊ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ጋዜጠኞች የየአገሮቹን ሉዓላዊነት እና ሕግ አክብረው መግባትና መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ጋዜጠኞች በሕጋዊ መንገድ ወደ አንድ አገር የሚገቡትን ያህል በሕገ ወጥ መንገድ ሊገቡ የሚችሉበት አጋጣሚም ሊከሰት ይችላል። በሕገ ወጥ መንገድ የሚገቡ ጋዜጠኞች የሚያጋጥማቸውን ችግርና ፈተና አስቀድመው ሊገነዘቡ ይችላሉ። በስውር ገብተው ሲያዙም የሚያጋጥ ማቸውን ፈተና ማስላታቸው አይቀርም።

በቅርቡ ማርቲን ካርል ሽብዬና ጁሃን ክርል ፕርሰን የሚባሉ ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞች የኢትዮጵያን ድንበር በሕገ ወጥ መንገድ ጥሰው በመግባት በኢትዮጵያ መንግሥት አሸባሪ ተብሎ ከተፈረጀውና ራሱን የአጋዴን ብሔራዊ ነጻ አውጪ ግንባር (አብነግ) ተብሎ ከሚጠራው ድርጅት ጋር ሆነው ሲንቀሳቀሱ መያዛቸው ይታወሳል።

ጋዜጠኞቹ በቁጥጥር ሥር ውለውና ጉዳያቸው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሦስተኛ ወንጀል ችሎት ታይቶ ባለፈው ወር አያንዳንዳቸው በ11 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ተፈርዶባቸዋል።

መንግሥት በሁለቱ ጋዜጠኞች ላይ የወሰደውን ሕጋዊ እርምጃ አስመልክቶ አንዳንድ ወገኖች የጋዜጠኝነት ሙያ የሚጋፋና ጋዜጠኞች በነጻነት እንዳይንቀሳቀሱ የሚያግድ እንዲሁም የመረጃ ነፃትን የሚያፍን ተግባር አድርገው መግለጫዎችን ሲያወጡ ሰንብተዋል።

እኔም የሙያው አካል ነኝና በግለሰቦቹ ላይ የተወሰደው እርምጃ እውነት የጋዜጠኝነትን ሙያ የሚጋፋ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ጉጉት አደረብኝ። ግለሰቦቹ እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ሁኔታና የፍርድ ሂደት መከታተሉንም ተያያዝኩት። ከሚወጡት ዘገባዎችና መንግሥት ከወሰደው እርምጃ በመነሳት የዘርፉ ምሁራንና የጋዜጠኛ ማህበራት በጉዳዩ ዙሪያ ምን አስተያየት እንዳላቸውም ከእነርሱ ጋር አጭር ቆይታ አደረኩና ይህንኑ ላካፍላቸሁ ወደድኩ።

ስዊድናውያኑ ጋዜጠኞች ሙያው የሚፈቅደውን ሥነ ምግባር ተከትለው አለመስራታቸውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ቤት ዲን ዶክተር ገብረመድኅን ስምዖን ያስረዳሉ። ግለሰቦቹ በትክክል በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ ተሰማርተው የሚሰሩ ከሆኑ በሕጋዊ መንገድ ወደ አገሪቱ በመግባት የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘት ይችሉ እንደነበረም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት የሰፈነባት አገር መሆና ይታወቃል ያሉት ዲኑ በሕገ ወጥ መንገድ የገቡት ጋዜጠኞች በቁጥጥር ሥር የዋሉበት ቦታም የጋዜጠኞችን ትኩረት የሚስብና የማጭት ዘገባ ሊያሰራ የሚችል አለመሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ይልቅ የጋዜጠኞቹን ትኩረት ሊስብ የሚገባው አልሻባብ በሶማሊያ በሚፈጥረው ማተራመስ ለረሀብ የተጋለጡ የሶማሊያ ዜጎችን ችግር መዘገብ ቢሆንም የተመረጠ እንደነበርም ጠቁመዋል፡፡ በጋዜጠኞቹ ላይ የተሰጠው የፍርድ ውሳኔ መረጃ የማግማገኘት መብታቸውን የሚነካ እንደሆነ ተደርገው የሚወሧጡ ዘገባዎች ከእውነት የራቁ መሆናቸውን አብራራርተዋል።

ፎቶ፡ከኢንተርኔት

ግለሰቦቹ የተከሰሱት በሕገ ወጥ መንገድ የአገሪቱን ሉአላዊነት ጥሰው በመግባታቸው ብቻ በአገሪቱ ሕግ መጠየቃቸው ዓለም አቀፍ አሰራር መሆኑንም ገልጸው፣ ከነጻ ፕሬስ፣ ሀሳብን በነጻነት ከመግለጽ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ አለመሆኑን፣ ጋዜጠኞቹን በሕገ ወጥ መንገድ እንዲገቡ የላካቸው የመገናኛ ብዙሃን ድርጅትም ግለሰቦቹ በፈጸሙት ድርጊት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቢከሰስ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የገንዘብ ቅጣት ሊፈረድበት እንደሚችል ያብራራሉ። የስዊድን መንግሥትም ለግለሰቦቹ በፍርድ ቤት ጥብቅና ቆሞ ሊከራከር እንደማይችል ይገልጻሉ።

ጋዜጠኞች ብዙ ኃላፊነትን ተሸክመው የሚሰሩ በመሆናቸው ግለሰቦቹ የፈጸሙት ሕገ ወጥ ተግባር የጋዜጠኝነት ሙያ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይገባውና ግለሰቦቹ የፈጸሙት ተግባር ሕገ ወጥ ሆኖ ሳለ በጋዜጠኛ ስም በነፃ እንዲለቀቁ የሚደረገው ጥረት ተቀባይነት እንደሌለው በአጽንዖት ይናገራሉ።

በነጻ ፕሬስ ስም የሚደርስ ጥፋትን በመራ አለባብሶ ማስፍፍ ተገቢ እንዳልሆነም ዶክተር ገብረመድኅን አውስተው ሙያው ለሕገ ወጥ ተግባር መሸሸጊያ ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት አስረድተዋል። በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የሰፈሩ የዴሞክራሲ መብቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ የሚቻለው በአገሪቱ ውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ብቻ እንደሆነም ያላቸውን እምነት ገልፀዋል። በአገሪቱ የጋዜጠኝነት ሙያ ብዙ የሚቀረው ቢሆንም፤ ሙያውን የሚያሳድጉ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውንም አስምረውበታል።

«በመያው የተሰማሩ ሰዎች ለጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር ተገዥ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ መንቀሳቀስ የሚቻልባት አገር ናት። በግልም ሆነ በመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን የሚሰሩ ጋዜጠኞች የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚጥሱ ግለሰቦችን ድርጊት በጥብቅ ሊያወዛዙ ይገባል። በአጠቃላይ የግለሰቦቹ ድርጊት ከመረጃ ነፃነትና ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር የሚገናኝ አይደለም። በሕዝቡና በአገር ጥቅም ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችን ጋዜጠኞች ሊቃወሙ ይገባል» በማለት ዶክተር ገብረመድኅን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ መሠረት አታላይ በበኩሉ ማህበሩ ለጋዜጠኞች መብት መጣስ ጥብቅና የሚቆም ቢሆንም፤ የግለሰቦቹ ድርጊት የጋዜጠኝነትን ሥነ ምግባር የጣሰ በመሆኑ ምግባሩን የሚያከብሩና ከህሎት ያላቸው እንደሚያስብ ላቸው ያስረዳሉ።

እነዚህ ሰዎች በሕገ ወጥ መንገድ የአገር ሉአላዊነትን ጥሰው በመግባታቸው ብቻ በአገሪቱ ሕግ መጠየቃቸው ዓለም አቀፍ አሰራር መሆኑንም ገልጸው፣ ከነጻ ፕሬስ፣ ሀሳብን በነጻነት ከመግለጽ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ አለመሆኑን፣ ጋዜጠኞቹን በሕገ ወጥ መንገድ እንዲገቡ የላካቸው የመገናኛ ብዙሃን ድርጅትም ግለሰቦቹ በፈጸሙት ድርጊት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቢከሰስ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የገንዘብ ቅጣት ሊፈረድበት እንደሚችል ያብራራሉ። የስዊድን መንግሥትም ለግለሰቦቹ በፍርድ ቤት ጥብቅና ቆሞ ሊከራከር እንደማይችል ይገልጻሉ።

ጋዜጠኞች ብዙ ኃላፊነትን ተሸክመው የሚሰሩ በመሆናቸው ግለሰቦቹ የፈጸሙት ሕገ ወጥ ተግባር የጋዜጠኝነት ሙያ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይገባውና ግለሰቦቹ የፈጸሙት ተግባር ሕገ ወጥ ሆኖ ሳለ በጋዜጠኛ ስም በነፃ እንዲለቀቁ የሚደረገው ጥረት ተቀባይነት እንደሌለው በአጽንዖት ይናገራሉ።

በነጻ ፕሬስ ስም የሚደርስ ጥፋትን በመራ አለባብሶ ማስፍፍ ተገቢ እንዳልሆነም ዶክተር ገብረመድኅን አውስተው ሙያው ለሕገ ወጥ ተግባር መሸሸጊያ ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት አስረድተዋል። በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የሰፈሩ የዴሞክራሲ መብቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ የሚቻለው በአገሪቱ ውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ብቻ እንደሆነም ያላቸውን እምነት ገልፀዋል። በአገሪቱ የጋዜጠኝነት ሙያ ብዙ የሚቀረው ቢሆንም፤ ሙያውን የሚያሳድጉ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውንም አስምረውበታል።

«በመያው የተሰማሩ ሰዎች ለጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር ተገዥ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ መንቀሳቀስ የሚቻልባት አገር ናት። በግልም ሆነ በመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን የሚሰሩ ጋዜጠኞች የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚጥሱ ግለሰቦችን ድርጊት በጥብቅ ሊያወዛዙ ይገባል። በአጠቃላይ የግለሰቦቹ ድርጊት ከመረጃ ነፃነትና ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር የሚገናኝ አይደለም። በሕዝቡና በአገር ጥቅም ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችን ጋዜጠኞች ሊቃወሙ ይገባል» በማለት ዶክተር ገብረመድኅን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ መሠረት አታላይ በበኩሉ ማህበሩ ለጋዜጠኞች መብት መጣስ ጥብቅና የሚቆም ቢሆንም፤ የግለሰቦቹ ድርጊት የጋዜጠኝነትን ሥነ ምግባር የጣሰ በመሆኑ የሚወገዝ ነው ብሏል። እንዲሁም ግለሰቦቹ በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ ተሰማርተው ነው የተያዙት ብሎ ማህበሩ እውቅና እንደማይሰጥም ገልጿል።

ኢትዮጵያ ሰላም የሰፈነባት አገር መሆኗን የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሚያውቀው ጉዳይ ሆኖ ሳለ፤ በሕገ ወጥ መንገድ የአገሪቱን ሉዓላዊነት ጥሰው መግባታቸው እንደ ኢትዮጵያዊነቱ የሚያመዝው ጉዳይ እንደሆነም ገልጿል። አንድ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ ስዊድንን በሕገ ወጥ መንገድ ጥሶ ቢገባና በቁጥጥር ሥር ቢውልም አገሪቱ መንግስት ድርጊቱን በዝምታ የሚያልፈው እንዳልሆነም በምሳሌ ያስረዳል።

ጋዜጠኞቹ የእንድን ሉዓላዊት አገር ድንበር በሕገ ወጥ መንገድ ጥሰው እንዲገቡ የሚፈቅድ ዓለም አቀፍ አሰራር እንደሌለ ገልጾ፣ መንግሥት የወሰደው ሕጋዊ እርምጃ የመረጃ ነጻነትን የሚገድብ ተደርጎ በአንዳንድ ወገኖች መገለጹ ስህተት እንደሆነ አስረድቷል።

ግለሰቦቹ በሕጋዊ መንገድ ገብተው በሶማሌ ክልል ያለውን እንቅስቃሴ በተመለከተ መረጃ ማግኘት እንፈልጋለን ቢሉና መንግሥት ቢከለክላቸው በአገሪቱ የመረጃ ነጻነት ተገድቧል ብሎ መውቀስ እንደሚቻል ጠቅሶ፣ ሆኖም ግለሰቦቹ ይህን መሥመር ተከትለው ባለመምጣታቸው የፈጸሙት ሕገ ወጥ ድርጊት ምስክር ነው ብሏል።

ግለሰቦቹ በቁጥጥር ሥር ከመዋላቸው በፊት በአካባቢው ያገኙት መረጃ በሚሰሩብት የመገናኛ ብዙኃን ድርጅት በኩል ባለመቅረቡ ግለሰቦቹ በጋዜጠኝነት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል ብሎ ለመናገር አያስችልም ሲል ጋዜጠኛ መሠረት አብራርቷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ የሚደርስበትን ጫና ፈርቶ ግለሰቦቹን ለፍርድ ሳያቀርብ ቢለቃቸው ኖሮ፤ የአገሪቱ የሕግ የበላይነት ትዝብት ላይ ሊወድቅ እንደሚችልና ዜጎች በፍትህ ሥርዓቱ ላይ እምነት እንዳያጡ ያደርግ እንደነበርም ተናግሯል።

ስለዚህ መንግስት የወሰደው ሕጋዊ እርምጃ በአገሪቱ የሕግ ልዕልና መኖሩን የሚያረጋግጥ እንደሆነ ያመለክታል። የግልም ሆነ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች የአገሪቱን ገጽታ ለማበላሸት የተለያዩ ወገኖች የሚያወጡትን መሠረተ ቢስ ዘገባና የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሊያውዝት ይገባል። የአገሪቱን የነጻ ፕሬስ እንቅስቃሴ በተመለከተ ጥብቅና መቆም የሚገባቸው ዜጎቿ ብቻ መሆን እንዳለባቸውም ይጠቁማል። ማህበሩ የጋዜጠኝነት ሙያ ለሌላ ድብቅ ዓላማ መጠቀሚያ ሊሆን እንደማይገባም በፅኑ ያምናል ብሏል።